# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው - ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋደ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)
P. O. Box 3198 . 10364 Stockholm 3 . Sweden . e-mail: meisone@t-online.de

| ዓመት 28 | ቁጥር 1 |
|---|---|

መጋቢት 1994

## ከባህር በር እስከ ሀገር ህልውና ትግላችን «ግንጥል» ትግል እንዳይሆን!!

በኢትዮጵያና በኤሪትራ መካከል አዲስ የሰላም ምዕራፍ ይከፍታል የተባለለት የሄጉ የድንበር ሽምግለና ኮሚቴን ከወዲሁ በጸረ ህዝቦቹ ወያኔና ሻእቢያ ምስጢራዊ ስምምነት የተደረሰበትንና የባእድ ሃያላን ቡራኬ ያገኘውን ውሳኔ ሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ይገልጻል። ኢትዮጵያ ከዚህ ብያኔ ምን ታገኛለች? ምንም አታገኝም። ይነስም ይብዛ ሽህ ኪሎሜትር ካሬ ይሁን ደርዘን ሺህ ኪሎሜትር ካሬ፣ ዘለዓለማቸውን የኢትዮጵያ የነበሩ ግዛቶች የተወሰነ ክፍል ለኤርትራ ታስረከባለች። በሽህም ይሁን በደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሳይወዱ፣ ሳይፈቅዱ ዜግነታቸውን ተነጥቀው ኤርትራውያን ናችሁ ይባላሉ። የሕዝቦች መብት ከመቸውም ይበልጥ ክቡር ነው በሚባልበት በዛሬው ዘመን ቅኝ ገዥዎች ከመቶ ዓመት በፊት አፍሪካንና ሕዝቦችዋን ሲቃረጡ ይጠቀሙበት በነበረው ሂደት ህዝቦች ሃሳባቸው ሳይጠየቅ ማንነታቸው ይበየናል። ሃያላን መንግሥታት ቤት ዘግተው እየተደራደሩ ወረቀት ላይ በሚያስመሩት «ድንበር» መሰረት አንተ ናጀሪያ፣ አነተ ካመሩን፣ አንተ ጋና፣ አንተ ቶጎ፣ አንተ ሴኔጋል ፣ አንተ ማሊ ውሰጥ ተካትተሃል ይሉ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም መቶ ዓመት ወደኋላ ሄደን በአገር በቀል ከሃዲዎች ትብብር ሃያላን ባእዳን በነካ አጃቸው ያንድ ሃገር ዜጎችንና፣ ቤተሰቦችን ሳይቀር እየነጣጠሉ «እናንተ በኢትዮጵያውነት ቀጥሉ፣ እናንተ ደግሞ ከዛሬ ጀምራችሁ ኢትዮጵያዊነታችሁ ተገፎ ኤሪትራዊ ሆናችኋል» ብለው ሊበይኑ የሚችሉበት ዘግናኝ ወጥመድ ወስጥ ገብተን እንገኛል።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ከሌሎች የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃየሎች ጎን በመቆም ከሻቢያ እበሪተኛ ወረራ ጀመሮ ይህ ጦር ጠማሽ ሃይል በጉልበት ከያዛቸው ግዛቶች ጦሩን አውጥቶ አለኝ የሚለውን የይገባኛል ጥያቄ ሰነስርአት ባለው ዘዴ በፍርድ መድረክ እንዲያቀርብና የኢትዮጵያና የኤርትራ ወጣቶች ከአውዳሚ ጦርነት እንዲተርፉ ታግሏል። መኢሶንም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ይህን አካሄድ ሲመርጡ መነሻ አድርገው ያነሷቸው አንዳንድ መሰረ.ታዊ መነደርደሪያዎች ነበሩ።

በዚህ ሰላማዊ የሙግትና የደርድር መድረክ ላይ ቆሞ ከታሪክ ሃቆች፣ ከአለም አቀፍ ህግ፣ ከህዝብ መብት ጥያቄዎች፣ ከሃገር ክብርና ጥቅም እየተነሱ መከራከርና ፍትህን መሻት እስከተቻለ ድረስ ኢትዮጵወያን ወንድማማች ህዝቦችን የሚያወድም ጦርነት ውስጥ ሳትገባ መብቷን ሙሉ በሙሉ ታስከብራለች የሚል ጽኑ እምነት ስለነበራቸው ነው። ይህ ግን አልሆነም ።

ለኮሚሽኑ «ብያኔ» መንደርደሪያ እንዲሆኑ የቀረቡት ሰነዶች ኢትዮጵያ በዚያ አስከፊ የቅኝ ግዛት መስፋፋት ዘመን ኮሎንያሊስቶች አፍሪካን ሲቃረጡና ህዝቦቿን ሲሸነሽኑ ከግዛቶቿ ና ከህዝቦቿ የቻለችወን አያተረፈች፣ ያልቻለችውን ደግሞ ልቡዋ እየደማ በ «ድንበር ውል» ለማስረከብ በግድ ከተፈራረመቻቸው በርካታ ሰነዶች መሃከል ከሁሉ ጎጂ የሆኑት ሶስት ወሎች ተመርጠው ነው ። እነዚህ ሶስት ውሎች በሃይል በማይመጣጠኑ ወገኖች መሃከል የተደረጉ ወሎች ስለሆኑ፣ በቪየና ኮ ንቬንሽንም ሆነ በሌሎች ዓለም አቀፍ መሰረት ተቀባየነት የላችውም። አነዚህ ውሎች ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ሲወር የተባሉትን ድንበሮች በአንድዮሽ እርምጃ ሰላፈረሳቸው፣ አሁንም በዓለም አቀፍ የውሎች ህግ መሰረት በሌላው ወገን ላይ አሰገዳጅነታቸው አክትሟል፣ እነዚህ ውሎች ኮሎኒያሊስት ጣሊያን በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ድል ከተመታች በኋላ ሙሉ በሙሉ ፈርሰዋል፣ አነዚህ ውሎች በአድ ክፉ የታሪክ አጋጣሚ የአፋርን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት ሰርዘዋልና የዚህን ህዝብ ዛሬም ያው የሆነ የኢትዮጵያዊነት ህልም ለዘለዓለም ሊሰርዙ አይችልም፣ እያልን የኢትዮጵያን ጥቅምና ህጋዊ መብት ጥያቄዎች እያነሳን መሟገት አንችላለን። እንሟገታለን። የዚህ ክርክርና ሙግት ዋናው አላማ የኢትዮጵያን ህዝብ ክህደት እንደተፈጸመበት ተገንዝቦ ለሃገሩ፣ ለመብቱና ለክብሩ ለመታገል እንዲነሳ ለማድረግ ሰንጂ በአልጀርሱ ውል መሰረት አሰራሩና ስልጣኑ ሲወሰን በወያኔና ሽቢያ ሴራ ሆን ተብሎ እጅ አግሩን ከታሰረ ኮሚሽን ምንም ነገር ጠብቀን አይደለም ። ሊዚህ የመጀመሪያው ምክንያት ኮሚሽኑ በአሰራሩ ክፍ ብለን የጠቆምናቸውንም ሆነ ሌሎች የተለያዩ አቋሞችን የሚያንጸባርቁ የተሊያዩ ወገኖችን መረጃዎች ከማዳመጥ የታገደ ኮሚሽን መሆኑን ነው። ወያኔዎች የሚከራከሩት በግፈኖቹና ሞተው በተቀበሩት ውሎች አንቀጾች አተረጓገም ላይ ነው። ሻእቢያዎችም ደግሞ በነዚሁ ውሎች መሰረት ጣልያኖች ነድፈውልናል በሚሏቸው ካርታዎች እንዳኝባዮች ናችው። እኛ አገር ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ደግሞ የፍትህና የህዝቦች መብት ይረጋገጥ፣ የዓለም አቀፍ የውሎች ህጋጋት (ሎው ኦፍ ትሪቲስ) ይከበሩ፣ በነዚህ ክርክሮች ላይ የተመረኮዘ የሃገራችንን ተገቢ ጥቅምና ያካባቢውን ለላምና መረጋጋት የሚያረጋግጥ ፍትሃዊ መፍትሄ እንዲሰጥ ከተፈለገ ሌሎች መረጃዎች፣ ሌሎች መከራከሪያዎች መቅረብ አለባችው እንላለን። ወያኔና ሻእቢያ አሲረው ያቋቋሙት ኮሚሽን እነሱ መርጠው የሚያቀርቡለትን «መረጃ» ከመመርመርና ገፋ ቢል አነዚህን መረጃዎች ለመብራራት እንዲቻል አንዳንድ «ባለሙያዎችን» ከማማከር በስተቀር እንደኛ «ጉዳዩ ያገባናል» የሚሉ ሌሎች ወገኖችን የማዳመጥ መብት የለውም። ሁለት ወገኖች የማይሞግቱበት ኮሚሽን ነው።

ከዚህ ኮሚሽን ፍትህ መጠበቅ የማይቻልበት ሌላው ምክንያትም ግልጽ ነው። ይህ «የሽምግልና» ኮሚሽን በተአምር ወይም «በስህተት» የልሆነ ነገር እንዳይፈርድ «ርትአዊ መፍትሄ እንዳይሻ» የተከለከለ ኮሚሽን ነው። በአልጀርሱ ውል አንቀጽ 4 (2) ላይ በግልጽ በኮሚሽኑ ላይ የተጣለው አስገራሚ ገደብ «ኤግዜኦ ኤ ቦን» በሚለው መርህ መሰረት የመወሰን ሰልጣን አይኖረውም። ብሎ ይደነግጋል። የዚህ የአልጀርሱ ውል ኦፊሴል የአማርኛ ትርጉም የለውም። ፓርላሜንቱ ሳይቀር በዚህ ከባድ ሰነድ «የተወያየው» ሰነዱ በእንግሊዝኛ ታድሎ አንዳንድ አንቀጾቹ ከእንግሊዝኛው ከስር ከስሩ እየተተረጎሙለትና «ከዚህ ወል ኢትዮጵያ እንዴት እንደምትጠቀም» በማብራራት ተጠቅሞም በቀረበለት'ሰነድ ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም በወያኔ መሪዎች ይህንን ብዙውን ጊዜ እንዳለ በላቲን የሚጠቀስ የህግ መርህ እንዴት አርገው «እንዳብራሩት» አናውቅም። ትርጉሙ ግን የታወቀ ነው። «የሽምግልና ሽንጎ» የተባለው ኮሚሽን «አኮርዲንግ ቱ ዘ

ፐሪንስፐል ኦፍ ፌርነስ ኤንድ ጉድ»
ወይም በርትአዊነት መርህ ተነሳስቶ የመወሰን
ስልጣን የለውም ማለት ነው።

በዚህ አንቀጽ መሰረት ኢትዮጵያ ከዚህ
ኮሚሽን ፊት ቀርባ «ፍርድ» የምትጠይቀው
የሞቱና የተቀበሩ ግፈኛ የቅኝ ግዛት ወሎች
ዘለዓለማቸውን አይገዙኝም ብላ አለም አቀ
ፋዊ የውሎችን ህግ እየጠቀሰች ክርክር
እንድታቀርብ፤ በቅኝ ግዛት ውሎች ከተ
ነጠቁ በኋላ መልሰውም ለአምሳ አመት ያህል
ተጎናጽፈውት የነበረውን ኢትዮጵያዊነታ
ቸውን ያለውዴታ በግድ ለዘለአለም ሊነፈጉ
አይችሉም በማለት የአፋር ለጆችዋን የፍ
ትህና፤ የመብት ጥያቄ እንድታነሳ፤ ከዚህ
አልፎ ተርፎ ዛሬ ደግሞ በባድመ፤ ዛላአ
ንበሳ፤ ኢሮብ ቡሬ ሌሎች ልጆቿን የዜግነት
መብት የሚሰርዝ ውሳኔ ርእታዊነት ይጎድ
ለዋል፤ ሰላምና መረጋጋትንም አያመጣም ብላ
እንዳትከራከር በወያኔና ሻቢያ ሴራ እጅ
እግሯን ታስራ ነው ማለት ነው።

በዚህ ሴራ እሱም እንደሃገራችን እጅና እግሩ
የታሰረው ኮሚሽን የሚሰጠው ብያኔ
ፍትሃዊ ነው ወይስ አይደለም? በጦርነት
ለታመሰው ለዚህ አካባቢ ሰላምንና መረጋ
ጋትን ያመጣል ወይስ ለባሰ ትርምስ በር
ይከፍታል? ህዝቦችን ያቀራርባል ወይስ
ያናክሳል? የሚሉ ጥያቄዎችን የማንሳት
ተልእኮ የለውም። ባጭሩ ጥያቄው በመሰረቱ
የፍትህ ጥያቄ ሆኖ ሳለ የፍትሃዊ ፍርድ
ተልእኮ የሌለው ኮሚሽን ሁሉም የሚመኘ
ውን ሰላምንና መረጋጋት የሚያግዝ ውሳኔ
ለያመጣ ይችላል የሚለው የተመድና የአን
ዳንድ ሃያላን ባእዳን አስተተሳሰብ ከተጨ
ባጩ ሁኔታ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው
ለኢትዮጵያም ለኤርትርያም ህዝብ እጅግ
አደገኛ የሆነ ኢሉዥን ነው እንላለን።

ይህ ሁሉ አባባል ለተባለው ኮሚሽን፤
ለተባበሩት መንግሥታት፤ ለባእዳን ሃያላንና
ሰአለም አቀፍ ኮሚኒቲ ባጠቃላይ የኢትዮ
ጵያን ማስረጃዎችና መከራከሪያዎች እያ
ቀረብን አንከራከር፤ የተያዘው አቅጣጫ
አደገኛ መሆኑን ከመጠቆም ወደ ኋላ እን
በል ማለት አይደለም። መሟገት፤ መከራከር ፤
የኢትዮጵያን ድምጽ ማሰማት ይኖርብናል።
ግድ ደግሞ ይህ በአለም አቀፍ ደረጃ
የምናሰማው ጩኸት ወሱንነት እንዲገባ
ንም ያስፈልጋል። ትኩረታችን ከሁሉም
በላይ ራሳችንና ህዝባችን ላይ መሆን አለ
በት። ትኩረታችን ከባህር በር አልፎ የሃገ
ራችን ህልውና ጉዳይ መሆን አለበት። የኢት
ዮጵያችን ህልውና ራሱ በታሪኳ አይታና
ሰምታም በማታውቀው ሁኔታ ለምንና እን
ዴት አደጋ ላይ እንደሆነ ጠንቅቀን መገንዘብ።
ከዚያም ህዝባችንም ያለውን አደጋ እንዲ
ገነዘብ ብቻ ሳይሆን አገራዊና ሕዝባዊ ራዕይ
ያለው አማራጭ እንዳለ ተገንዝቦ ባለ በሌለ
ሃይሉ አደጋዎቹን ሁሉ ለመቋቋም ለራሱም ፤
ለሀገሩም ብሩህ የሆነ አማራጭ እንዲዋደቅ
ማድረግ ይኖርብናል ።

መኢሶን ዛሬ በባህበር በር ጉዳይ ከዳር እስከ
ዳር በመንቀሳቀስ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ
ከራዕይ አልባዎቹ ከነመለስ ዜናዊ ጋር በያ
ዘው ትንንቅ ውስጥ እሱም ሰለኢትዮጵያ
ችን ራእይ አልባ ሆኖዋል የሚል እምነት
የለው። ሁላችንም ብንሆን ይቺ አገር ከረ
ጅምና አኩሪ ታሪኳ፤ እንደቀስተ ደመና
ተሰበጣጥረው ከሚያሸበርቁ የህዝቦቿ ባህል፤
እነዚህ ልጆቿ ለዚች አገር ካላቸው ክብርና
ፍቅር፤ከአስተዋይነታቸውና ከታታሪነታቸው
የሚመጥን ኢኮኖሚ ገንብተው በሰላም፤
በማህበራዊ ፍትህና በዴሞክራሲ ተደጋግፈው
የሚኖሩባት አገር ትሆናለች የሚል የጋራ
ራእይ አለን ብለን እናምናለን። ይቺ ሰላማ
ዊት፤ ዴሞክራሲያዎትና ፍትሃዊት አገር
የማንም ሆነ የምንም ጥገኛ፤ ለማንም ሆነ ለም
ንም አጎብዳች ሳትሆን በአለም ህዝቦች ሸንጎ
የተከበረችና የታፈረች አገር የማረግ ራእይ
የሁላችንም ራእይ ነው እንላለን።

በሁሉም መስክ ከወደቅንበት አዘቅት ተነስ
ተን ወደዚህ ራእይ እንጓዝ ካልን ዛሬ በባህር
ጉዳይ የታየው የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ
አድማሱ ሰፍቶ ህዝባችንን ከዳር እስከዳር
በሚያካትት መልኩ መቀጠልና መፋፋም
ይኖርበታል። መኢሶን ዛሬ ሁሉም ኢትዮ
ጵያዊ እንዲገነዘበው የሚፈልገው ሃገራችን
ፊት ከባህር በር ማጣት የባሰ ችግርና አደጋ
እንደተደቀነ፤ ይህንን አደጋ በሚገባ አጢነን
ልንዋጋ ካልተነሳን ወይም ደግሞ ትኩረትና
ቅደሚያ እየተምታታ የኛንም የህዝባችንንም
ጉልበትና ወኔ ካሰበጣጠርን ኢትዮጵያ እንደ
ሃገር ህልውናዋ ፈተና ላይ የሚወድቅበት
ህዝባችን በፍትህ እጦት ከሰውነት ውጭ
የሚሆንበት አደጋ አለ።

ዛሬ ሁሉም የሚቀበለውና የሚተቸው የወያኔ
ዎችን ፖለቲካ ስርአተ ኢሰብአዊነት፤ የፖለ
ቲካ ራእያቸው ኪሳራና ጸረ ኢትዮጵያዊነት
ነው። በመኢሶን እምነት እነዚህ አጥፊ ሃይ
ሎች አዲሱን አለም አቀፋዋ የግሎባላይዜ
ሽን ግፈኛ ስርአት እየታከኩ ለጥቅማቸውና
ለጸረ ኢትዮጵያ አላማቸው ሲሉ በሀገራችን
በመትከል ላይ ያሉት «የነጻ ገበያ» ተብየ
ልቅ የኢኮኖሚ ስርአትም ከዘረኛ የፖለቲካ
መዋቅሮቻቸውና ፖሊሲዎቻቸው በባሰ እንጂ
ከነዚህ ባላነሰ ሁኔታ ጸረ ኢትዮጵያ የኢኮ
ኖሚና ማህበራዊ ስርአት ነው።

ይህንን ተገንዝበን ብሄራዊ ኢኮኖሚ
ለመገንባት የሃገራችንን ነጋዴ ፤ ኢንቬስተርና
አምራች የሚጠብቅ የሚንከባከብ ብሄራዊ
የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከሌለ፤ ሰራተኛውን የመ
ዋቅር ማስተካከያ ፖሮገራም፤ ፕራይቬ
ታይዜሽን ወዘተ እያለ ለጅብ የሚዳርግ
ፖሊሲ ከቀጠለ፤ ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ
በተባለው አዲስ ፈሊጥ ይበልጥ የብሄራዊ
ኢኮኖሚ ግንባታ ህልማችን «ነጻ» የሆነ ገበያ
የሚሉት ስርአት ወስጥ የእውር የድንብ
ራቸንን ከተዘፈቅን፤ በማዳበሪያና በመ
ደሃኒት ስም በበለጸጉት አገሮች የተከለከሉ
ኬሚካሎች የጥቂት ድንበር ዘለል ኩባን
ያዎች ጥቅም ለማዳበር እየተባለ ወደ ሃገር
እየገቡ ድሃውን ገበሬ ለእዳ፤ መሬታችንን ለብ
ክለትና ለውድመት እያጋለጡን፤ የትምህርት፤
የጤናና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች
ባለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ትእዛዝ
«ለገበያ ሃይሎች» ትተን እቅድ በሌለው
ሁኔታ እየተደናበርን ማህበራዊ ቀውሶችን
ማባባሳችንን ከቀጠልን፤ ባጭሩ ወያኔዎች
እየተከሉብን ያለው ጸረ ኢትዮጵያ የኢኮኖ
ሚና ማህበራዊ ስርዓት ለኢትዮጵያችን ያለ
ንን ራእይ የሚጻረር እደገኛ ስርአት አርገን
በመቁጠር ልንታገለው ካልተነሳን አገራችንም
ህዝባችንም ወደጥፋት እየነጎዱ እንደሆነ
መገንዘብ ይኖርብናል።

በዚህ ጉዳይ የብዙ ቅን ዴሞክራቶችና አገር
ወዳዶች ክረክር ይገባናል። ዛሬ የቅድሚያ
ቀደሚያ መስጠት ያለብን ይህንን ጸረ ኢትዮጵያ
ሃይል አስወግደን «ኢትዮጵያዊ ራዕይ ያለው»
መንግሥት ለማቋቋም ለሚ ደረገው ትግል ነው
የሚል ክርክር አለ። «ኢትዮጵያዊ ራዕይ ያለው
መንገስት» በሚለው እኛም እንስማማለን።
ችግሩ እዚህ ላይ ሳይሆን ይህንን አጥፊ ሃይል
ለማስወገድ የሚደረገው ትግል እስከዛሬ
እንደታዘብነው በአንድ በኩል በጥቂት
ከሃዲዎችና በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂት
ግንባር ቀደም ዴሞክራትና አገር ወዳ ዶች
መሃከል ከመሃል ዘልቆ በሚሊዮን የሚቆጠሩ
የሃገራችንን ገበሬዎች፤ ሰራተኞች፤ ነጋዴዎች፤
ኢንቨስ ተሮች፤ አምራቾች እንዲያካተት
ምን እናድ ርግ? የሚለው ጥያቄ ነው።
መልሱ ለኛ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው።
በርእዩተ አለም ምርጫም ሆነ፤ በጥራት
ማጣት በባዕዳን ሃያላን ላይ አጉል ተስፋ
በመጣልም ሆነ ህዝባችንን ወጥረው የያዙት
የኢኮኖሚና የማህብራዊ ችግሮች «ነገ እሸን
ፈን ዴሞክራሲ ሲሰፍን እንያያዛቸዋለን »
ከሚል አጉል ስሌት ተነስትን በመካሄድ ላይ
ያለውን ጸረ ወያኔ ትግል «ግንጥል» ትግል
አድረገነዋል። የወያኔን አገዛዘ ነጻ ምርጫ፤ የህግ
የበላይት፤ ብሄራዊ ወይይት እያልን የፖሊቲካ
አማ ራጮች ይዘን ስንፋለም በዚህ አጥፊ ሃይል
እየተተከለ ኢትዮጵያን እንደ አገር፤ ህዝባቸንን
እንደሰብአዊ ፈጡር ህልውናቸውን እየተፈታ ተነ
ካለው ስርዓት አኳያ «ለህዝባችን ማህበ ራዊ ፍትህ፤
ለአገር ግንባታ፤ ለብሄራዊ ኢኮኖሚ» ወዘተ እያልን
ጸረ ኢትዮያ ለሆ ነው የወያኔዎች የኢኮኖሚና
ማህበራዋ ስር አት አማራጭ አቅርበን እየታገልን
አይደ ለም።

ይህንን ዘላቂነት ያለው አገር አድን አማ ራጭ
አንግበን ህዝባችንን በዚህ አማራጭ ዙሪያ
አሰባስበን እስካልታገልን ድረስ አንድ ጊዜ ነጻ
መርጫ፤ ሌላ ጊዜ ብሄራዊ እርቅና ወይይት፤
አሁን ደግሞ እነደምናየው የባህር በር በሚሉ
አጅግ ቁምነገር ቢኖራቸውም ከጠቅላላው የነፃት
ተግላችን ውስጥ ሳይካተቱ እስከቀረቡ ድረስ
በኢትዮጵያ ህዘብና በጠ ላቶቹ መሃከል ወሳኝና
ዘላቂ የሃይል ሚዛን ለመፍጠር በማያበቁ
ጥያቄዎች ዙሪያ አንድ ሰሞን በወኔና በጋለ የትግል
መንፈስ እን ሳለን። ያ ወኔና የትግል መንፈስ
ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ ይበርዳል። ትግላችን ዘላለ
ሙን «ከርሞ ጥጃ» ይሆናል። ከዚህ አዙሪት
ወጥተን ለዚች አገር ወደምናልምላት ብሩህ እጣ
ፈንታ በያንዳንዷ ቀን ይበልጥ እየተቃ ረብን
የምንሄደው ለዚህ ጸረ ኢትዮጵያ የፖ ለቲካ፤
የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሥርዓት ሁለ ገብና
አጠቃላይ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህ በራዊ
አማራጭ ይዘን ስንጓዝ እንጂ ዛሬ አንድ መፈክር፤
ነገ ሌላ የትግል ጥሪ እያስ ተጋባን የተዋጣለት
አንድ ወጥና ሁለገብ ስርአታቸውን በተነጣጠሉ
ትግሎች ስንፋለም ስላይደለ ፤ ለኢትዮጵያ
ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ተጨባጭ አማራጭ
አቅርበው ለህዝ ባችን የትግል አቅጣጫ
እንዲያመለክቱ ጥሪ ያችንን እናስተላልፋለን።
ከባህር በር እስከ አገር ህልውና ደረስ ያለው ሰፊና
አስችጋሪ የትግል መስክ በግንጥል መልኩ
ከተካሄደ የትም እንዳላደረሰንና የትም
እንደማያደርስ ያለፈው የትግል ጉዟችንም
ሆነዛሬ ያለን በት ሁኔታ በግልጽ አሳይቶልና።